# ፕሬሱ የተቃዋሚውን ጓንት ማጥለቅ ሲጀምር ባያስፈራም ያሳፍራል፡፡

ነሲቡ ታየ 08/20/09

አንድ አመት በቀረው ምርጫ ዋዜማ ላይ እንገኛለን፡፡ ምርጫ በተቃረበ ቁጥር የፖለቲካ ሃይሎች የተለያየ እንቅስቃሴ ማድረጋቸው የተለመደ ነው፡፡ ይህን በመሰለው የምርጫ ዋዜማ ላይ ቁም ነገረኛ ፓርቲዎች የመወደደሪያ ማኒፌስቶ ያወጣሉ፡፡ ቅልብጭ ያሉና የሚያማልሉ ቃልኪዳኖችን ያሰማሉ፡፡ ከመራጩ ጋር ይገናኛሉ፡፡ ምንም የሚጨበጥ መርሃ ግብር የሌላቸው ደግሞ አንዳንዶች በቀልድ መልክ እንደሚሉት ወንዝ በሌለበት ድልድይ እንሰራለን እስከማለት ይደርሳሉ፡፡ በዘንድሮው ምርጫ ይህን ለማየት ያለን ተስፋ ትንሽ ይሁን ትልቅ ባላውቅም ከተቃዋሚዎች አንዳንዶቹ ያሉበትን ሁኔታ በማጤን ወንዝ በሌለበት ድልድይ እሰራለሁ የሚል ተቃዋሚም እንዳናጣ መጨነቅ ጀምሬያለሁ፡፡ የለምክንያት አይደለም፡፡ አብዛኞቹ ተቃዋሚዎች እየተባሉ፣ እየተበላሉ በተገኘችውም ዴሞክራሲ ለመጠቀም ሃላፊነት የማይሰማቸውና አንዳቸው ሌላቸውን የጐሪጥ የሚመለከቱ መሆናቸው በይፋ መታየት ስለጀመረ ነው፡፡ የአዲስ ነገር ጋዜጣ /ስምን ሰይጣን ያወጣዋል አሉ! /አንድ አምደኛ ከኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በኋላ በግምንቱ አንድነት ፓርቲ ሆኗል በማለት እስከመግለጽ እንደደረሰው ሁሉ ፓርቲዎቹ እየተባሉ ነው፡፡ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መሪዎችን እንዳረጋጋው ሁሉ አንድነትንም ጣልቃ ገብቶ ያረጋጋ አለማለቱ ተመስገን፡፡

የተቃዋሚው ጐራ መባላት ያለ፣ የነበረና የሚኖር ይመስለኛል፡፡ አባላቱ በጥላቻና በኋላቀር አላማ የተሰበሰቡ በመሆናቸው የተቃዋሚው ጐራ ዛሬና ነገ ብቻ ሳይሆን ከርሞም መባላቱ አይቀርም፡፡ ይህ ካልሆነ ከምላሴ ፀጉር

ይነቀል፡፡ በዛሬው ፅሁፌ ተቃዋሚዎች ዋነኛ ሳይሆን የስላች ትኩረት እንዲኖራቸው ያደረግኩት እንዲያው ከንቀት ወይም ከሌላ አተያይ ሳይሆን ሰሞኑን አንድነት ፓርቲ ያወጣውን መግለጫ ነካክቼ በተቃዋሚው ጐራ ያሉት ፓርቲዎች መስቀል ያማራቸውን ጓንት በማጥለቅ ላይ ወዳሉት ሚዲያዎች ለመረማመድ ስለፈለግኩ ብቻ ነው፡፡ አንድነት ፓርቲ የራሱ የስም ግዝፈት ተጭኖት ከሁለት ለዚያውም ከውስጥ በመነጨ መፈንዳት ሲተረከክ የተመለከትነው ከተመሰረተ መንፈቅ ሳይሞላው ነው፡፡ ታዲያ እርስ በርሱ በመናቆር ላይ ያለው አንድነት ሰሞኑን ገዥው ፓርቲ ይህን አደረገኝ፣ ያንንም ደገመኝ የሚል መግለጫ ማውጣቱን አነበብን፡፡ “ጉድ ነሽ የአንኮበር ቅጠል፣ በየሄድሽበት ነገር ማንጠልጠል” አሉ፡፡ /ተረቱ የአፄ ምኒሊክን አልጋ ወራሾች ለማስቆጣት እንዳልሆነ ይመዝገብልኝ/ ለመሆኑ አንድነት የት አለና ነው ገዥው ፓርቲ አንድነትን የሚያዋክበው፡፡ የአንድነት የልብ ወዳጅ /ሮል ሞዴል/ የሆኑት ጓድ መንግስቱ ተስፋ በቆረጡበት በአንድ ወቅት “ጓዶች! አሁን እኛ አለን ይባላል? ምኑን አለነው! በቁም ሞተናል’ኮ “እንዳሉት አንድነትም በቁሙ ሞቷል፡፡ ታዲያ ገዥው ፓርቲ እንዴት እንዴት አድርጐ የሌለን ፓርቲ ለማዳከም ይሰራል፡፡ ይህ የፈጠራ ድርሰት ብቻ ነው፡፡ አንድነት ፓርቲ በህይወት ካለም ፕሮፌሰር መስፍን “ አሰራሩ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ሆኗል ” ስላሉ በርግጠኛነት በአንድነት ላይ የሚሰነዘር ጥቃት ከኒዮ ሊበራሎቹ ካልሆነ በአንድ “ጐራ” ከተፈረጀው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጐራ የሚመጣበት ሊሆን አይችልም፡፡ ስለዚህ ኢህአዴግን ለቀቅ ፕሮፌሰር መስፍንን ጠበቅ ማድረግ ይበጅ ይመስለኛል፡፡ እንደሰሞኑ ዜና ከሆነ ኢህአዴግ ለፓርቲዎች የሚከፋፈል ብር እንጂ ፓርቲዎችን የሚከፋፍል ፖለቲካ ይዞ መጣ ሲባል አልሰማንም፡፡ እናም የሚከፋፍላችሁን ውስጣዊ ምክንያት ፈትታችሁ እንኳን ለአንድነት ለብዙነት የሚበቃውን ገንዘብ በስምምነት ለመቀራመት መዘጋጀቱ ይበጃችኋል፡፡ እንዲያው ንስሃ ልግባና አንዳንዴ እኔስ ብሆን አነስተኛ ጥቃቅን እያለኩ እሴት ፈጠራ ላይ ደፋ ቀና ከምል አንድነት፣ ህብረት፣ ቅንጅት እያልኩ ከትንሽ ሱቅ የተሻሉ ፓርቲዎችን መስርቼ በዘመንኛው ቋንቋ ከኪራይ ሰብሳቢነቱ ጠበል ጠዲቅ ብቀምስ ይሻለኝ ነበር ይሆን የሚል ሃሳብ ይጎበኘኛል፡፡ ፖለቲካውስ አላስማማችሁም፣

የምትወዱት ገንዘብ ሊያስማማችሁ ይችል እንደሁ ብሎ ነው ትንሽ ጥቆማ ቢጤ ማቅረቤ፡፡

የፓርቲዎቹ ነገር በይፋ ባያበቃም ነገረ ስራው ግን ያለቀለትና ያበቃ ይመስላል፡፡ ይህን ጋዜጦች ተገንዝበዋል፡፡ ስለዚህም ፓርቲዎቹ ፎጣ ለመወርወር አስበዋል በሚል ስሌት ጋዜጦች የፓርቲዎቹን ጓንት እያጠለቁ ይገኛሉ፡፡ የጋዜጦች የሰሞኑ ትኩረት ገዥውን ፓርቲ በውርጅብኛቸው ቁም ስቅል ማብላት ነው፡፡ ኢህአዴግ  ውሾቹ ይጮሃሉ ግመሉ ግን ጉዞውን ቀጥሏል በሚለው የአረቦች ተረት እየተመራ ስራውን ይሰራል ወይስ ለጋዜጠኛ ተቧቃሾች ምላሽ ይሰጣል የሚለው ጥያቄ ፈረንጆች የሚሊዮን ዶላር ጥያቄ ነው የሚሉት አይነት ነው፡፡ አዲስ ነገሮች እንደሚሉት ኢህአዴግ እብድ ከሆነ የግመል ጉዞውን ትቶ ምላሽ ይሰጥ ይሆናል፡፡ አሊያም ተቃዋሚ ጋዜጦች በራሳቸው እንደበት ወይም ብእር እንዳሉት ኢህአዴግ እብድ ሳይሆን የቤት ስራውን ሰርቶ ያጠናቀቀ ድርጅት ከሆነ አጥር ላይ ተቀምጦ የመሳቅ ፋንታ የሱ መሆኑ ነው፡፡

በዚያው ሰሞን ሪፖርተር በፃፈው ርእስ አንቀፅ የኢህአዴግን አፍንጫ፣ ፀጉር፣ ጥርስ፣ ሆድ፣ ቁርጭምጭሚትና ጣፊያ ሁሉ በሽተኛ አድርጎ በድምር አንድ ሃሙስ የቀረው አስመሰለው፡፡ ይህን የሪፖርተር ርእሰ አንቀፅ ሂልተን ሆቴል ላይ አንድ ጥግ ይዤ እያነበብኩ እያለ በርስ በርስ መናቆር ብስክስኩ የወጣው ፓርቲ መሪ የሆኑና ማእረጋቸው ኢንጅነር ይሁን ዶክተር ለጊዜው የተዘነጋኝ ሰው ብቅ አሉ፡፡ ሴት አትመራኝም ያሉት ዶክተር ሳይሆኑ ኢንጅነር በላቸው ይመስሉኛል፡፡ / የኢንጅነሩን ስም የቀየርኩት አንድም በኮፒ ራይት እንዳልጠየቅ አለያም ግዛቸው፣ ሽጣቸው፣ ለውጣቸው የሚሉ ስሞች የዘመነ ግሎባላይዜሽን የንግድ ቋንቋዎች እንጅ የፖለቲከኛ መጠሪያ ሲሆኑ ስለሚያስፈራኝ ብቻ ነው፡፡/ የጁቸ አብዮት መሪ ለመሆን እየተዘጋጁ ያሉት እኝህ ታላቅ ሰው በአጠገቤ በማለፍ ላይ ስለነበሩ ድምፄን ከፍ አድርጌ ከሪፖርተር ርእሰ አንቀፅ ቆንጥሬ "ኢህአዴግ ታሟል ብዬ" አነበብኩና አሰማኋቸው፡፡ መጀመሪያ የቀልዴን መስሏቸው ግራ የመጋባት ፊት

ባይታይባቸውም ብዙ ሳይቆዩ ተረጋግተው “ እስኪ ድገመው ሲሉኝ” ከልባቸው መሆኑ ገባኝና ከፈለጉ ጋዜጣውን እንዲያነቡ አቀበልኳቸው፡፡

ኢንጅነሩ ከኔ ወስደው የጋዜጣውን ርእሰ አንቀፅ አነበቡት፡፡ እንደዚያ አይነት መልካም ዜና ሰምተው የሚያውቁም አልመሰሉኝ፡፡ ጮቤ ረገጡ፡፡ ጋዜጣውን ወደልባቸው አስጠግተው “በርግጥ ኢህአዴግ ታሟል! አይ ሪፖርተር እናት አንተን የመሰለ ሸውከኛ ብቻ ትፍጠር” እያሉ ዘለሉ፡፡ ሞባይላቸውን አውጥተውም ለድርጅቱ ፀሐፊ ርእሰ አንቀፁን አነበቡላቸው፡፡ “…በቃ አንድ ሃሙስ ነው የቀረው አትጠራጠር፣ ፈፅሞ ከኛ ጋር የማይነፃፀር በሽታ ነው፡፡ እ …የኛ’ኮ ቀልድ ነው፡፡ የስጋ ትል የዘመድ ጥል ታውቅ የለ … እ … እንዳሱ ነው፡፡” ሪፖርተር “ኢህአዴግን ከራስ ጠጉር እስከ እግር ጥፍሩ ታሟል ሲለው እኛን አንድ ሃሙስ ቀርቷችኋል መች አለን፡፡ ሪፖርተር’ኮ ነቢይ ነው፡፡ አንዴ ከተናገረ ከቃሉ ዝንፍ የሚል ነገር የለም ” ብለው አስደሰቷቸው፡፡ አከታትለውም “በል እንግዲህ ኢህአዴግ የሚያጋልጥ አንድ መግለጫ በፍጥነት አውጣ” የሚል ቀጭን ትእዛዝ ሰጥተው ጋዜጣዬን እንደያዙ በደስታ እየተፍነከነኩ እንደጓድ ሊቀመንበር ወደፊት …!፡፡ በማግስቱ ከአንድነት ፓርቲ የተሰጠ መግለጫ በየጋዜጣው ላይ የሪፖርተር ምክርና መመሪያ በተቃዋሚዎች ላይ እንዴት ፈጥኖ እንደሚሰርፅ ለመገንዘብ ቻልኩ፡፡ እናት ሪፖርተርን ወለድኩ ትበል፡፡

ሪፖርተር ፓርቲዎቹን ተክቶ ከገዥው ፓርቲ መፋለም ጀምሯል፡፡ እግዜር ጉልበቱን የሰንበሌጥ ሳይሆን የዝሆን፣ እጁን በሶ ሳይሆን ድንጋይ የጨበጠ ያድርግልን! አሜን፡፡ ከአዲስ ነገርማ ታድያ ምን ይጠበቃል፡፡ በዚያው ሰሞን ራሱ ጋዜጣ ሆኖ አንዱን ሚዛናዊ አካሄድ አለው ብሎ የጠረጠረውን ጋዜጣ እንዳይሆን አድርጎ ሲያደባየው አንብቤ ገርሞኝ ነበር፡፡ አዲስ ነገር ተቃዋሚዎችን ተክቶ ዘገር እየነቀነቀ ወደ ጐራው መግባቱን ሳላጤን ጋዜጦች የራሳቸው ፓርቲ ሳይኖራቸው የፓርቲዎችን ያህል አቋም እንዴት ሊይዙ ይችላሉ ብዬ መጠየቅ ጀምሬ ነበር፡፡ አሁን ግን በርግጥም ሆኗል፡፡ ሪፖርተር “አዲስ ነገር የተቃዋሚ ፓርቲን ተክቶ ተቃዋሚ ይሆናል” ብሎ ባይተነብይም

“የፈሩት ይደርሳል፣ የጠሉት ይወርሳል” እንዲሉ አዲስ ነገር ከሚዛናዊነት ርቆ…… በጣም ርቆ ወደ ፓርቲ ልሳንነት ተሸጋግሯል፡፡ አንቂ፣ ቀስቃሽና አደራጅ ልሳን! በመወዳደሪያ ቀለበቱ መሃል ላይ ሆኖ በገለልተኝነት ለማፋለም ሳይሆን ጓንቱን አጥልቆ አንድ ማእዘን ላይ ቆሞ በትይዩ ከተሰለፈው ኢ.ህአዴግ ጋር ሊቀጣቀጥ ከመዘጋጀት አልፎ መቀጣቀጥም ጀምሯል፡፡ በትንቢተ ሪፖርተር አንድ ሃሙስ የቀረው ኢ.ህአዴግ ከተቻለ እርስ በርሱ ተናክሶ የተበጣጠሰውን የተቃዋሚ ጎራ ሰዓታት ቆመው ማህሌት ገብተው ምለው ተገዝተው በአንዳች አይነት ምትሃት ህይወት ሊዘሩበትና ለበትረ ስልጣን ሊያበቁት ይህ ካልተቻለም ዋናውን ተቃዋሚ ድርጅት ሊተኩ በተነሱ ወጣት ዲያቆናት ከተገነባው አዲስ ነገር ከተረፈ መቼም ታሪክ ነው፡፡ በጠሃዩ ንጉስ በሃይለስላሴ ስም እንይዘዋለን እንጅ “ በሽተኛው” ኢ.ህአዴግ ማሸነፍ የለበትም፡፡ ለምን የቀረ ገኸ ፓርቲ አይቀርም፡፡ ተቃዋሚዎች የቃታቸውን ታሪክ የመስራት ጀብዱ የነሱን ህልም ተረክበው፣ ራእያቸውን አንግበው፣ በገንዘብ ሳይሆን በእናት አገር ፍቅር ነደው የሚንቀለቀሉት ጋዜጦቻችን ይሰሩታል ብለን ተስፋ እናደርግ ዘንድ ይፈቀድልን፡፡

ይህን ፅሁፍ ስከትብ አንደ ሃሙስ ቀርቶታል የተባለው ኢ.ህአዴግ ስንት ሃሙስ እንዳሳለፈ ለማስላት ሞከርኩ፡፡ ድርጅቱን እኔ ከማውቀው ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ያለውን እንኳ ሳሰላው 18x52 መሆኑ ነው፡፡ ጳጉሜን ጨምሮ 954 ሃሙሶች መሆኑ ነው፡፡ ቀበሮ የበሬ “እንትን” ይወድቃል ብላ ስትከተል ኖረች አሉ አበው፡፡ የቅንጅትን መነሻና መድረሻ

ደግሞ ከዚህ አነፃፀርኩት፡፡ 1x52 መሆኑ ነው፡፡ ለዛውም ቅንጅት መንፈሱ ሙሉ አመት ከደፈነ፡፡ ስለዚህ ኢ.ህአዴግን “እንኳን ከሟረተ ከወረወረም” የሚያድነው አንድ ሃይል አለ ማለት ነው፡፡ የበሬ “እንትን” ይወድቃል ብለው ሲከተሉ የሚኖሩት ሪፖርተርና አዲስ ነገር የማይገባቸው ሃይል፡፡ ለኔ ይህ ሃይል አንዳች አይነት ልዩ ነገር ሳይሆን ኢ.ህአዴግ ደጋግሞ መስመሬ የሚለው ነገር ያጎናፀፈው ሃይል ይመስለኛል፡፡ ተቃዋሚዎች ፎጣ ወደ መወርወሩ

እየተቃረብን ነው ሲሉ እነሪፖርተር ጓንቱን ማጥለቃቸው ባያስፈራም ያሳፍራል ያልኩት የሚዛናዊነትና ገለልተኝነትን ጭንብል አሽቀንጥረው ጥለው የተከበረውን የጋዜጠኝነት ሞያ በማራከሳቸውና በቀበሮዋ ከንቱ ምኞች ከተፈጥሯዊ አካሉ ተገንጥሎ የሚወድቅ እንትን ስለሌለ ብቻ ሳይሆን ኢህአዴግ የቀየሰው መስመር ብርቱ ስለሆነም ነው፡፡

አስተያየት ለሚሰጠን sofiateshome@yahoo.com